# መብቶችዎን ይወቁ

በዩናይትድ ስቴትስ በመሥራት ላይ ሳሉ ስለሚኖሩዎ መብቶች የሚያብራራ በራሪ ፅሁፍ።

ብሔራዊ የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር በማንኛውም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥ ስልክ
1-888-373-7888 (በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ)











# መብቶችዎን ይወቁ

በዩናይትድ ስቴትስ የሚኖርዎ ቆይታ ብዙ የሚጠቀሙበት እንደሚሆን ልበ ሙሉ ነን። ሆኖም ግን መጥፎ ሁኔታዎች ቢከሰቱ፣ መብቶች አሉዎት፣ እገዛ ማግኘትም ይችላሉ!

## ከዚህ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡-

- ፍትሐዊ ክፍያ የማግኘት
- ከመድልዖ ነጻ የመሆን
- ከወሲብ ትንኮሳና ብዝበዛ ነጻ የመሆን
- ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ የማግኘት
- ከሠራተኛ ማኅበር፣ ከኢሚግራንትና ከሠራተኞች መብት  ተከራካሪ ቡድኖች እገዛ የመጠየቅ
- ስቃይ የመላበትን የሥራ ሁኔታ ትቶ የመሄድ

**እንግልት የደረሰብዎ እንደሆነ ለብሔራዊ የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር በማንኛውም ግዜ የሚሰራ ስልክ ቁጥር 1-888-373-7888 ያሳውቁ (በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ)፣ በ233733 "HELP" ብለው በስልክ ቴክስት ይላኩ ወይም በ *NHTRC@POLARISPROJECT.ORG* የኢሜል መልዕክት ይላኩ።**

**ከ200 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች እገዛ ለማድረግ ሁሌም ዝግጁ የሆኑ የሰለጠኑ  ባለሙያዎች አሉ። የራስዎን ሥም ወይም ማንነት መግለጽ አይጠበቅብዎትም። የበለጠ ለማወቅ *WWW.TRAFFICKINGRESOURCECENTER.ORG*ን ይጎብኙ።**

ያሉት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ከሆነ፣ በስልክ ቁጥር 911 ለፖሊስ ይደውሉ (በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ)። ያጋጠመዎት አጣዳፊ ሁኔታ ምን እንደሆነ፣ እርስዎ የት እንዳሉ እና እርስዎ የሚደውሉበትን የስልክ ቁጥር ይንገሯቸው። የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማይናገሩ ከሆነ፣ አስተርጓሚ እንዲዘጋጅልዎ ይጠይቁ። ፖሊሶች እርስዎ ካሉበት ሲደርሱ ይህንን በራሪ ፅሁፍ  ሊያሳዩዋቸውና ስላጋጠመዎት  እንግልት ሊነግሯቸው ይችላሉ።

የ A-3፣ G-5፣ H፣ J፣ NATO-7፣ ወይም የቤት ውስጥ ሰራተኛ B-1 ኢሚግራንት ቪዛ ካለዎት፣ በቪዛ ቃለ ምልልስ ጊዜ ይህን በራሪ ፅሁፍ መቀበል አለብዎ። የቆንስላ መኮንኑ እርስዎ ቪዛውን ከማግኘትዎ በፊት ይህንን በራሪ ፅሁፍ ማግኘትዎን፣ ማንበብዎንና መረዳትዎን ማረጋገጥ አለበት። ካላገኙ ግን፣ የቆንስላ ኦፊሰሩ በራሪ ፅሁፉን መስጠትና በእርሱም ላይ ከእርስዎ ጋር ውይይት ማድረግ አለበት። በተጨማሪ በበራሪ ፅሁፉ ላይ ስለሰፈረው መረጃ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎ ለጥያቄዎችዎ መልስ መስጠት አለበት።

# የቪዛዎ ሁኔታ ምንም ዓይነት ቢሆን ያለዎት መብት

መብቶቼ ተጥሰዋል ብለው ካመኑ፣ ለመንግሥት መስሪያ ቤት፣ ለሠራተኞች ማኅበር፣ መንግሥታዊ ላልሆነ ድርጅት ወይም ለሌላ እገዛ ሊያደርግልዎ ለሚችል ድርጅት ማመልከት ይችላሉ። የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር የማይችሉ ከሆነ፣ አስተርጓሚ እንዲመደብልዎ ይጠይቁ።

## 1. ፍትሐዊ ክፍያ የማግኘት መብት ያለዎ ስለመሆኑ

- ለሚሰሩት ሥራ በሙሉ ክፍያ የማግኘት መብት አለዎት።
- ለአብዛኛዎቹ የሥራ ዓይነቶች ቢያንስ በፌዴራል መንግሥት የተቀመጠውን አነስተኛ ክፍያ የማግኘት መብት አለዎት። በአሁኑ ወቅት ተፈጻሚነት ያለውን የፌዴራል አነስተኛ ክፍያ ለማወቅ የሚከተለውን ይመልከቱ፡- www.dol.gov/whd/minimumwage.htm
- ከዚህ የሚከተለውን ሁኔታ አሟልተው ከተገኙ የፌዴራል መንግሥት ካስቀመጠው አነስተኛ የክፍያ መጠን በላይ የማግኘት መብት አለዎት፡-
    - የሚኖሩት ከፍ ያለ የአነስተኛ ክፍያ መጠን ተፈጻሚ በሚሆንበት ስቴት፣ ከተማ ወይም ካውንቲ ከሆነ፣
    - የቅጥር ውልዎ/የቪዛ ፕሮግራም ከፍ ያለ ክፍያ መከፈል እንዳለበት የሚጠይቅ ከሆ፣
- በሳምንት ከ40 ሰዓታት በላይ ለሚሰሩት ሥራ ለተጨማሪዎቹ የሥራ ሰዓታት በሰዓት የሚከፈልዎ መደበኛ ደመወዝ በአንድ ከግማሽ ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ይከፈልዎ ዘንድ ባለመብት ነዎት። ለምሳሌ መደበኛ ደመወዝዎ በሰዓት $10 ከሆነ፣ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከ40 ሰዓታት በላይ በሥራ ላይ ለሚሆኑባቸው ጊዜያት አሠሪዎ ለእያንዳንዱ ሰዓት $15 መክፈል ሊኖርበት ይችላል።
- አሠሪዎ ከሚሰጥዎ የክፍያ ቼክ ላይ ገንዘብ ከቀነሰ፣ ይህ ተቀናሽ ተብሎ ይታወቃል። አሠሪዎ ከክፍያ ቼክዎ ላይ የሚቀነሰውን እያንዳንዱን ተቀናሽ በግልጽ መለየት ወይም ማሳወቅ አለበት።
- ከደመወዝዎ ላይ ተቀናሹ መጠን ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ገንዘብ በሕግ ከተቀመጠው የደመወዝ ተመን በታች ከሆነ ቅናሹ ሕገወጥ ሊሆን ይችላል። አሠሪዎች ብዙውን ጊዜ የደንብ ልብስ፣ የደህንነት መጠበቂያ መሣሪያዎች፣ አስፈላጊ መሣሪያዎች፣ አቅርቦቶች ወይም የቅጥር ክፍያ ተቀናሽ አያደርጉም። ለአንዳንድ ቪዛ አይነቶች መኖሪያ በነፃ መስጠት አለበት።
- ሕጋዊ ተቀናሾች የሚባሉት እርስዎ የሚመርጧቸው፣ ለምሳሌ እንደ ጤና ኢንሹራንስ፣ የሠራተኛ ማኅበር ክፍያ ወይም ቅድሚያ ደመወዝ ያሉ ተቀናሾች እንዲሁም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ለሕጻን ልጅ ቀለብ ወይም ለትዳር አጋር የገንዘብ ድጋፍ ወይም በክስረት የፍርድ ሂደት ምክንያት በአሠሪው መቀነስ ያለባቸው ተቀናሾች ናቸው። ጥቂት ልዩ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው፣ በዩናይትድ ስቴትስ የሚሰሩ የኢሚግራንት ያልሆነ ቪዛ ያላቸው ሰዎች የፌዴራል እና የስቴት የገቢ እና የቅጥር ግብር መክፈል አለባቸው። እርስዎ እና አሠሪዎ ከደመወዝ ክፍያዎ ላይ የገቢ ግብር በቀጥታ ተቀናሽ

**ጠቃሚ መረጃ፡-** ለወደፊት ማጣቀሻነት እንዲረዳዎ ይህንን በራሪ ፅሁፍ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ይዘውት ይምጡ።



**ጠቃሚ መረጃ፡-** በቆይታዎ ላይ ተመስርቶ፣ በዩናይትድ ስቴትስ በሚቆዩባቸው ጊዜያት የጤና ኢንሹራንስ እንዲኖርዎ ሊያስፈልግ ይችላል። ከዚህም ሌላ የጤና ኢንሹራንስ ወጪ ለመቀነስ እንዲረዳዎ የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት መብት ሊኖርዎ ይችላል።

እንዲደረግና በአሰሪው እንዲያዝ ልትስማሙ ትችላላችሁ። በጠቅላላው አሠሪዎ የቅጥር ግብር፣ ለምሳሌ እንደ ማሕበራዊ ደህንነት እና የሜዲኬር ግብር የመሳሰሉትን ከደመወዝዎ ላይ በቀጥታ ተቀናሽ በማድረግ አሰሪው ሊይዝ ይችላል።

## 2. ከመድልዖ ነጻ የመሆን መብት ያለዎ ስለመሆኑ

- አሠሪዎ በዕድሜዎ (ዕድሜዎ 40 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ)፣ በጾታዎ፣ በዘር፣ በብሔር ወይም በጎሳ፣ በቆዳ ቀለም፣ በኃይማኖት፣ በጄኔቲክ መረጃ (የቤተሰብ የጤና ታሪክን አካትቶ) ወይም በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት በሥራ ቦታ እርስዎን በተለየ ወይም በመጥፎ ሁኔታ ቢይዝ ወይም ቢያሰራ ይህ ድርጊት ሕገወጥ ነው።
- ሴት ስለሆኑ ወይም ነፍሰ ጡር በመሆንዎ፣ ልጅ በማጥባት ላይ ስላሉ ወይም ነፍሰ ጡር ሊሆኑ ይችላሉ በሚል እሳቤ እርስዎን በተለየ ሁኔታ መያዝ ወይም ማሰራት አይችልም።

## 3. ከወሲባዊ ትንኮሳ ወይም ከወሲብ ብዝበዛ ነጻ የመሆን መብት ያለዎ ስለመሆኑ

- አሠሪዎ በእርስዎ ላይ ወሲባዊ ትንኮሳ መፈጸም አይችልም። አሠሪዎ ምንም ዓይነት ወሲባዊ ትንኮሳ የመላበት ወይም ፀያፍ የሆነ ፆታዊ አስተያየት መስጠት አይችልም።
- አሠሪዎ በእርስዎ ላይ የወሲብ ብዝበዛ ቢፈጽም ይህ ሕገወጥ ነው፤ ክልከላ ከተደረገባቸው እነዚህ ተግባራት መካከል፡-
  - ማንኛውንም ወሲባዊ ተግባር እንዲፈጽሙ አጥብቆ መጠየቅ፤
  - ወሲባዊ በሆነ መልኩ እርስዎን መንካት፤
  - ማንኛውንም የወሲብ ድርጊት እንዲፈጽሙ እርስዎን በኃይል ሊጠቀሙ፣ ሊያታልሉዎ ወይም ሊያስገድዱዎ ይችላሉ።

## 4. ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ እንዲኖርዎ መብት ያለዎ ስለመሆኑ

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚሰሩ እንደመሆኑ መጠን፣ ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ቦታ እንዲኖርዎ ባለመብት ነዎት፤ ከዚህም ጋር የሚከተሉት የተካተቱ ይሆናሉ፡-

**ጠቃሚ መረጃ፡-** ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመምጣትዎ በፊት ከውጭ አገር ዜጎች ሠራተኞች ድርጅቶች ወይም ከቀድሞ የውጭ አገር ሠራተኞች ምክር ለማግኘት ይሞክሩ። እነርሱም እርስዎ በዩናይትድ ስቴትስ ባሉባቸው ጊዜያት ችግሮች ቢያጋጥሙዎ ወይም ጥያቄዎች ካሉዎ ሊያናግሯቸው የሚችሏቸውን ሰዎች ወይም ድርጅቶች ስሞችና ስልክ ቁጥሮች ሊሰጡዎ ይችላሉ።



- **ሕክምና፡-** ከሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳቶችና ሕመሞች ለአሠሪዎ የማሳወቅ መብት አለዎት። በሥራ ቦታ ላይ ሳሉ ጉዳት ከደረሰብዎት ወይም ከታመሙ፣ ሕክምና እንዲደረግልዎ ሊጠይቁ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ አሠሪዎ ከሥራ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳቶች ወይም ሕመሞች ነጻ ሕክምና ያመቻቻል፣ በጉዳት ላይ በነበሩበት ጊዜ ያጡትንም ደመወዝ በከፊል ይከፍላል። በሚሰሩበት ግዛት የሠራተኞች ካሣ ማመልከቻ ማቅረብ ሊኖርብዎ ይችላል።
- **ከአደጋ መጠበቂያ መገልገያዎች፡-** እርስዎ የሚሰሩት በጸረ-ነፍሳት መድሃኒት ወይም አደገኛ በሆኑ ኬሚካሎች ላይ ወይም በዚያ ዙሪያ ከሆነ፣ አሠሪዎ ለሥራው የሚያስፈልጉ ከአደጋ መጠበቂያ መገልገያዎች (ለምሳሌ መተንፈሻ ወይም ጓንት) ማቅረብ እና ለእነርሱም የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን አለበት።
- **ሥልጠና፡-** በሥራ ቦታዎ ላይ አደገኛ ስለሆኑ ነገሮች፣ ጉዳትን ለማስቀረት ስለሚረዱ ዘዴዎች እንዲሁም በሥራ ቦታዎ ተግባራዊ ስለሚደረጉ የደህንነት እና የጤና ደረጃዎች መረጃና ሥልጠና ማግኘት አለብዎ። ሥልጠናው ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋና ቃላት ሊሆን ይገባል።
- **መኖሪያ ቤት፡-** አሠሪዎ መኖሪያ ቤት የሚሰጥ ከሆነ፣ መኖሪያ ቤቱ ንጹህና ደህንነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት። ከሥራ ሰዓታት ውጪ በሆኑ ጊዜያት ከቤትዎ ለመውጣት ፈቃድ ሊሰጥዎ ይገባል።
- **መታጠቢያ ቤቶች፡-** መታጠቢያ ቤቶች ንጹህና ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል። አሠሪዎ እንደአስፈላጊነቱ ወደ መታጠቢያ ቤት እንዲሄዱ መፍቀድ አለበት።
- **የመጠጥ ውሃ፡-** ንጽህናው የተጠበቀ የመጠጥ ውሃ የማግኘት መብት አለዎት።
- **ሳሙናና ንጹህ ውሃ፡-** እንደአስፈላጊቱ በተለይ ደግሞ ጸረ-ነፍሳት/ኬሚካሎች እንዲሁም ጸረ-ነፍሳት መድሀኒት የተረጨባቸውን አትክልት ወይም ፍራፍሬዎች ከነኩ በኋላ እንዳስፈላጊነቱ እጆችዎን በውሃና በሳሙና የመታጠብ መብት አለዎት።
- **ድንገተኛ ሕመም፡-** ወጪዎችዎ ሊሸፈኑ ይችሉ ይሆናል፣ ስለዚህ አሠሪው አስፈላጊውን የወረቀት ሥራ እንዲያከናውንና እንዲያቀርብ በተቻለ ፍጥነት ስላጋጠመዎት ጉዳት ወይም ሕመም ለአሠሪዎ ማሳወቅ አለብዎት። በሐኪም ዘንድ፣ በክሊኒክ ወይም በሆስፒታል በሚገኙ ጊዜ፣ ስለደረሰብዎ ጉዳት ወይም ስለሕመምዎ የማስረጃዎች ቅጂዎች እንዲሰጡዎ ይጠይቁ።



ሥራዎ በቀጥታ በጸረ-ነፍሳት መድሀኒቶች ወይም አደገኛ በሆኑ ኬሚካሎች ላይ ወይም በዚያ ዙሪያ ከሆነ፡-

- እርስዎ የሚሰሩባቸው ኬሚካሎች ባሕርይ ምን እንደሆነ የማወቅ መብት ያለዎ ከመሆኑም በላይ አሠሪዎ ደመወዝዎን እየከፈለ በሥራ ቦታዎ ላይ ስላሉ ኬሚካሎች ሥልጠና ሊሰጥዎ ይገባል።
- የት እና መቼ ጸረ-ነፍሳት መድሀኒቶች እንደተረጩና የተጋላጭነትን አደጋ ለማስወገድ መቼ ኬሚካሉ ወደተረጨበት ቦታ መግባት ችግር እንደማያስከትል አሠሪዎ ሊነግርዎ ይገባል። ጸረ-ነፍሳት መድሀኒት በመረጨት ላይ ወዳለበት ስፍራ ከመግባት ይቆጠቡ።

## 5. ከማኅበር፣ ከኢሚግራንትና ከሠራተኞች መብት ተሟጋች ቡድኖች እገዛ የመጠየቅ ምብት ያለዎት ስለመሆኑ

- የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ከሥራ ባልደረባዎችዎ ጋር በጋራ በመሆን አሠሪዎ ደመወዝዎን ወይም የሥራ ሁኔታዎችን እንዲያሻሽል የመጠየቅ መብት አለዎ። አብዛኞቹ ሠራተኞች በሥራ ቦታ የሠራተኛ ማኅበር የመመስረት፣ አባል የመሆን እና እንዲህ ያለውን ማኅበር የመደገፍ መብት አላቸው።
- በሥራ ላይ ባልሆኑባቸው ጊዜያት የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግና በሥራ ቦታዎች የሥራ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ለመጠየቅ በሚደረጉ ሕዝባዊ ንግግሮች፣ ጉዞዎችና ሰልፎች ላይ ተሳትፎ ማድረግ ይችላሉ።
- ይህ መብት በእርስዎ የኢሚግሬሽን ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አይደለም። መብቶችዎን በመጠየቅዎ ምክንያት አሠሪዎ በእርስዎ ላይ እርምጃ መውሰድ አይችልም።

## 6. እንግልትን የሚያስከትል የሥራ ሁኔታን ለቅቀው የመሄድ መብት ያለዎት ስለመሆኑ

- እንግልት እየደረሰብዎ ከሆነ ሊያደርጉት የሚችሉት እጅግ አስፈላጊ ነገር ቢኖር ደህንነትዎን ማረጋገጥ ነው። አሠሪዎ በእርስዎ ላይ መጉላላትን እያደረሰብዎ ከሆነ፣ በሥራዎ ላይ መቆየት አይጠበቅብዎትም።
- አሠሪዎን ትተው ቢሄዱ የቪዛዎ አገልግሎት የሚያበቃ ቢሆንም እንኳን፣ የቪዛዎን ሁኔታ ወይም አሠሪዎን መቀየር ይችላሉ። ይህንን ለማድረግ ዩናይትድ ስቴትስን ለቅቀው መውጣት ሊኖርብዎ ይችላል። የቪዛዎ አገልግሎት ቢያበቃ እንኳን፣ በእርስዎ ላይ እንግልትን የሚያደርሰውን አሠሪዎን ትተው ከሄዱ በኋላ ድጋፍ ሊያገኙ ይችላሉ።
- በሥራ ላይ ሳሉ ወይም አሠሪዎን ትተው ከሄዱ በኋላ በአሠሪዎ ላይ በይፋ የክስ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ይህን በማድረግዎ አሠሪዎ በእርስዎ ላይ እርምጃ ከወሰደ (ወይም የአጸፋ ድርጊት ከፈጸመ) አሠሪዎ ሕግን በመጣስ ላይ ነው ማለት ነው።

**ጠቃሚ መረጃ፡** - ከአሠሪዎ፣ ከተቋራጭ ወይም መልማይ የሚያገኙት የሕግ ምክር ገለልተኛ ላይሆን ይችላል። ስለዚህም የሕግ ምክር ሲፈልጉ ከገለልተኛ ጠበቃ ጋር ይነጋገሩ።

# በእርስዎ የኢሚግራንት ያልሆነ የቆይታ ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ተጨማሪ መብቶች

## A-3፣ G-5፣ NATO-7 እና B-1 የቤት ውስጥ ሠራተኞች

- አሠሪዎ በዩናይትድ ስቴትስ ህግ መሰረት ውሉን አዘጋጅተው ለእርስዎ መስጠት አለባቸው።
- በውሉ ውስጥ ለቤት ውስጥ ሠራተኛ የሚከፈለው የሰዓት ክፍያ ወይም ደመወዝ መጠን መገለጽ አለበት። የሰዓት ክፍያው በዩናይትድ ስቴትስ ፌዴራል መንግሥት፣ በግዛት ወይም በአካባቢው ሕግ ከተቀመጡት አነስተኛ የክፍያ መጠኖች መካከል የሚበልጠው ሊሆን ይገባል።
- አሠሪዎች እርስዎ በሚረዱት ቋንቋ ውሉን አዘጋጅተው መስጠት አለባቸው። የውሉን ሁኔታዎች መገንዘብዎን ያረጋግጡ፤ ውሉ ምን እንደሚል ካልተገነዘቡ ፊርማዎን አያኑሩ።

## ተጨማሪ መስፈርቶች ለ A-3፣ G-5 እና NATO-7 የቤት ውስጥ ሠራተኞች

ቢያንስ ቢያንስ በውሉ ውስጥ ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝሮችን ሊካተቱ ይገባል፦

- አሠሪዎ የዩናይትድ ስቴትስን ሕግጋት ለማክበር የተስማማ መሆኑን መግለጽ አለበት።
- ደመወዝ መቼ እንደሚከፈል፣ የአከፋፈሉ ሁኔታ፣ ሳምንታዊ የሥራ ሰዓታት፣ የበዓላት ቀናት፣ የሕመም ዕረፍትና የፈቃድ ቀናት፤ እና
- አሠሪዎ ፓስፖርትዎን፣ የቅጥር ውልዎን ወይም ሌሎች ግላዊ ንብረቶችዎን ከእርስዎ እንደማይደብቅብዎ መስማማቱን መግለጽ አለበት።

## H-2A የጊዜያዊ የግብርና ሠራተኛ ቪዛዎች

- ለሰራተኛ መልማይ ምንም ዓይነት ክፍያ መክፈል የለብዎትም።
- በሚረዱት ቋንቋ በጽሁፍ የተዘጋጀ የቅጥር ውል የማግኘት መብት ያለዎት ሲሆን፣ እንዲህ ባለው ውል ውስጥ ስለደመወዝ፣ የሥራው የጊዜ ርዝመት፣ ሰዓታት ጥቅማ ጥቅሞች (የትራንስፖርት፣ መኖሪያ፣ ምግብ ወይም የማብሰያ ስፍራን አካትቶ) እንዲሁም ከክፍያዎችዎ ላይ ስለሚደረጉ ቅናሾች መረጃዎችን መያዝ አለበት።
- በሚሰሩት ሥራ ልክ የሚከፈልዎም ቢሆን እንኳን ፍትሐዊ ክፍያ የማግኘት መብት አለዎት።
- በአሠሪዎ ዘንድ ለመስራት ጉዞ ሲያደርጉ ከተነሱበት ስፍራ ስራ ቦታው ላይ እስኪደርሱ የሚያስፈልግዎትን ትራንስፖርት ማቅረብ ወይም ለትራንስፖርቱና የውሎ አበል ወይም የሥራ ውሉን ከፊል ያህል ካጠናቀቁ በኋላ ለተጠቀሱት ነገሮች ያወጧቸውን ምክንያታዊ ወጪዎች ተመላሽ ሊያደርግልዎ ይገባል። የሥራ ውሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ አሠሪዎ ከሥራ ቦታዎ ወደመጡበት አካባቢ ለመመለስ የሚያስፈልግዎትን ትራንስፖርት ማቅረብ ወይም ለትራንስፖርትና ለውሎ አበል የሚያስፈልግዎትን ወጪ መሸፈን አለበት። ከደመወዝዎ ላይ የቪዛ ወጪዎች ሲቀነሱ ቀሪው ገንዘብ ከአነስተኛው የዩናይትድ ስቴትስ የደመወዝ መጠን ያነሰ ከሆነ፣ አሠሪዎ በመጀመሪያው የሥራ ሣምንት ወደ አገሪቱ ለመምጣት ያወጧቸውን የመጓጓዣና የቪዛ ወጪዎች ተመላሽ ማድረግ አለበት። ከዚህም ሌላ አሠሪዎ በአሠሪው ከተሰጠ መኖሪያ ወደ ሥራ ቦታ ለመጓጓዝ በነጻ ትራንስፖርት ሊያቀርብልዎ ይገባል።



**ጠቃሚ መረጃ፡** - አሠሪዎ በተገቢው ጊዜ ለእርስዎ ክፍያ መፈጸም አለበት። በዩናይትድ ስቴትስ እንደተለመደው ሠራተኞች በየሁለት ሣምንቱ ክፍያ ያገኛሉ።

- ከ H-2A ቪዛዎ ጋር በተያያዘ ለሰጧቸው አገልግሎቶች የዩናይትድ ስቴትስ የማሕበራዊ ዋስትናና የሜዲኬር ግብር ከመክፈል ነጻ ነዎት።
- በጠቅላላው አሠሪዎ በውሉ ጊዜ ከተጠቀሰው አጠቃላይ ጊዜ ውስጥ ከ¾ የሥራ ቀናት ጋር እኩል ለሆኑ የሥራ ሰዓታት ሊያሰራዎ ይገባል።

## H-2B ጊዜያዊ ከግብርና ውጪ የሌላ ሥራ ሠራተኛ ቪዛዎች

- በምንም መልኩ ለሠራተኛ መልማይ ክፍያ መክፈል የለብዎትም።
- በሚረዱት ቋንቋ የሥራ ትዕዛዝ በፅሁፍ ሊደርስዎ ይገባል። በሥራ ትዕዛዙም ውስጥ ስለደመወዝ፣ የሥራ ጊዜ ርዝመት፣ ሰዓታት፣ ጥቅማ ጥቅሞች (ትራንስፖርት፣ መኖሪያ ቤት፣ ምግብ ወይም የምግብ ማብሰያ ስፍራዎች) እና ከደመወዝዎ ላይ ስለሚደረጉ ቅናሾች ዝርዝር መረጃ ሊኖር ይገባል።
- በጠቅላላው አሠሪዎ በእያንዳንዱ የ12 ሣምንታት ጊዜ ውስጥ ከ¾ የሥራ ቀናት ጋር ተመጣጣኝ ለሆኑ የሥራ ሰዓታት ሊያሰራዎ ይገባል።
- በሰሩት ሥራ ልክ የሚከፈልዎ እንኳን ቢሆን፣ ክፍያዎ ፍትሐዊ ሊሆን ይገባል።
- አሠሪዎ ከውጭ አገር ተጓጉዘው ለመምጣት የሚችሉበትን ትራንስፖርት መክፈል ወይም የውሉን ጊዜ በከፊል ሲያጠናቅቁ ወደ አገሪቱ የተጓዙበትን የትራንስፖርት እና የውሎ አበል ወጪዎች ተመላሽ ማድረግ አለበት። በተጨማሪም የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ ወይም ከመጠናቀቁ በፊት በማናቸውም ምክንያት ከሥራ የተሰናበቱ እንደሆነ ወደ አገርዎ የሚመለሱበትን ወጪ እና የውሎ አበል መክፈል አለበት። ከደመወዝዎ ላይ የቪዛ ወጪዎች ሲቀነሱ ቀሪው ገንዘብ ከአነስተኛው የዩናይትድ ስቴትስ የደመወዝ መጠን ያነሰ ከሆነ፣ አሠሪዎ በመጀመሪያው የሥራ ሣምንት ወደ አገሪቱ ለመምጣት ያወጧቸውን የመጓጓዣ እና የቪዛ ወጪዎች ለእርስዎ መክፈል አለበት።

## J-1 የልውውጥ ጎብኚ ቪዛዎች

- የጸደቀው DS-2019 የመርሃ ግብር ቀናትዎን፣ የልውውጡን ምድብ፣ የስፖንሰርዎን ሥምና የልውውጥ መርሃ ግብርዎ የሚከናወንበትን አስተናጋጅ አካል ያብራራል።



- ስፖንሰርዎ የልውውጥ መርሃ ግብርዎን አስመልክቶ ያሉትን ወጪዎች፣ ሁኔታዎችና ገደቦች ሁሉ በትክክል ማብራራት አለበት።

### የበጋ ወቅት የሥራ ጉዞ

- ቀደም ብለው ያገኙት ሥራ ከሌለ፣ በዩናይትድ ስቴትስ እንደደረሱ ስፖንሰርዎ ሥራ እንዲያገኙ እገዛ ሊያደርግልዎ ይገባል።

### በሥራ ላይ ተለማማጅ ወይም ሰልጣኝ

- ስፖንሰርዎ በአካል፣ በስልክ ወይም በዌብ ካሜራ ቃለ መጠይቅ ሊያደርግልዎ ይገባል።
- ስፖንሰርዎ የተለማማጅ ወይም የሰልጣኝ ምደባ ዕቅድ (DS-7002) ሊሰጥዎ የሚገባ ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ የሚያገኙት ማናቸውም ገቢና የሥልጠና መርሃ ግብሩ ዓላማዎች ማጠቃለያ መካተት አለባቸው። በሳምንት ቢያንስ የ32 ሰዓታት ሥራ ሊሰጥዎ ይገባል።
- ስፖንሰርዎ ስለሚያጋጥሙዎ ወጪዎችና ሊከፍሏቸው ስለሚገቡ ክፍያዎች እንዲሁም በዩናይትድ ስትቴትስ በሚኖርዎ ቆይታ ስለሚያስፈልግዎ የኑሮ ወጪ በጽሁፍ የተዘጋጀ መግለጫ ሊሰጥዎ ይገባል።
- ስፖንሰርዎ የጤና ኢንሹራንስ ማቅረብ ወይም እንዲህ ላለው ሽፋን መክፈል ባይኖርበትም እንኳን የጤና ኢንሹራንስ ማግኘትዎን ማረጋገጥ አለበት።

### የውጭ አገር ዜጋ ሆኖ ማደሪያና ምግብ ለማግኘት የቤት ውስጥ ሥራ የሚሰራ/የምትሰራ ሰው፡-

- የሚያስተናግድዎ ቤተሰብ በድኅረ ሁለተኛ ደረጃ ተቋም እንዲመዘገቡና ትምህርት እንዲከታተሉ ማድረግና ለትምህርቱም እስከ $500 መክፈል አለበት።
- በቀን ከ10 ሰዓታት ወይም በሳምንት ከ45 ሰዓታት በላይ መስራት አይጠበቅብዎትም።
- አማካሪዎ ከእርስዎና ከሚያስተናግድዎ ቤተሰብ ጋር በየጊዜው መገናኘት አለባቸው።

**ጠቃሚ መረጃ፥** - ጉዞ ከማድረግዎ በፊት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችዎን በተለይም የፓስፖርትዎን፣ የዩናይትድ ስቴትስ ቪዛዎን፣ የሥራ ውልዎንና ተጨማሪ መታወቂያ ሰነዶችዎን ሁለት ቅጂዎች ያዘጋጁ። የእያንዳንዱን አንድ አንድ ቅጂ በአገርዎ ለሚያምኑት ሰው ይስጡ፣ ሌሎቹን ቅጂዎች ደግሞ ከእርስዎ ጋር ይያዙ።




# የኢሚግራንት ያለሆነ ቪዛዎ

ለኢሚግራንት ያልሆነ ቪዛ የሚባለው በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የሚሰጥ ሰነድ ሲሆን፣ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የሚጓዙ ሰዎች ለአንዳች ዓላማ ወደ አገሪቱ ለመግባት ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፣ ለምሳሌ ለሥራ፣ ለትምህርት ወይም በባሕል ልውውጥ መርሃ ግብር ለመሳተፍ። በዚህ ሁኔታ በውጭ አገር ለሚገኝ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ የቪዛ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ። የኢሚግራንት ያለሆነ ቪዛ ካገኙ በኋላ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ መጓዝና ወደ አገሪቱ ለመግባት ፈቃድ እንዲያገኙ በዩናይትድ ስቴትስ ኢሚግሬሽን ኦፊሰር ዘንድ ሊቀርቡ ይችላሉ። የቪዛዎ የአገልግሎት ጊዜ ያበቃ እንደሆነ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በድጋሚ ከመግባትዎ በፊት አዲስ ቪዛ ማግኘት አለብዎ።

ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመግባት ፈቃድ ካገኙ፣ የኢሚግሬሽን ኦፊሰር በፓስፖርትዎ ላይ ማኅተም በማድረግ፣ በዚያም ላይ ለመግባት ተቀባይነት ያገኙበትን ቀን፣ ተቀባይነት ያገኙበትን ምድብ እና “እስከ



[የተወሰነው ቀን] መግባት ይችላሉ” በማለት ያሰፍሩበታል። የቪዛዎ ጊዜ እንዲራዘም በዩናይትድ ስቴትስ ሲቲዝንሺፕ ኤንድ ኢሚግሬሽን ሰርቪስስ ጥያቄ ካላቀረቡ በቀር በአገሪቱ ያለዎት ቆይታ ሕጋዊ እንዲሆን በI-94 የተገለጸው መቆየት የሚችሉበት የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ አስቀድመው አገሪቱን ለቀው መውጣት አለብዎ።



**ጠቃሚ መረጃ፡-** ዩናይትድ ስቴትስ ከደረሱ በኋላ ፓስፖርትዎንና ሌሎች የጉዞ ሰነዶችዎን ደህንነቱ በተጠበቀና ሁሌም ሊያገኙበት በሚችሉት ስፍራ ማስቀመጥ አለብዎ። አሠሪዎ ፓስፖርትዎን ቢወስድብዎ ይህ ሕገ ወጥ ተግባር ነው።

# የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር

የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎች ጥበቃና አገልግሎቶች የማግኘት መብት ያላቸው ከመሆኑም ሌላ አንዳንድ ሕዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር፣ ሕጻናትን ለወሲብ ንግድ መዳረግ፣ አዋቂዎችን በኃይል በወሲብ ንግድ ሥራ ማሰማራት፣ ማጭበርበር ወይም ማስገደድና ማንኛውንም ሰው በግዳጅ የጉልበት ሥራ ማሰማራት የታከለበት የወንጀል ድርጊት ነው። እንዲህ ያለው ብዝበዛ ፈጻሚዎች ማለትም ለምሳሌ ሕገወጥ የሠራተኞች አዘዋዋሪዎች፣ የወሲብ ደላሎችና የወሲብ ንግድ ገዢዎች በፌዴራልና በስቴት የጸረ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሕግጋት ስር ሊከሰሱ ይችላሉ። ሕገወጥ የሠራተኞችና የወሲብ አዘዋዋሪዎች የወንጀል ክስ ሊቀርብባቸውና በፍትሐብሔርም በኃላፊነት ሊጠየቁ ይችላሉ። ከዚህ የሚከተሉት የሰው ልጅ ሕገወጥ ዝውውር መኖሩን ሊያሳዩ የሚችሉ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ናቸው።

## ማስፈራራትና ፍርሃት

ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችና እነርሱን የሚረዱ ሰዎች እርስዎ ትተው እንዳይሄዱ ፍርሃት እንዲሰማዎ ማስፈራሪያና ሌሎች ተመሳሳይ ዘዴዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ። ለምሳሌ፡-

- ድብደባ፣ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት፤
- የድብደባ፣ የአካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ማስፈራሪያ፤
- ሠራተኞች የሥራ ወይም መኖሪያ ሥፍራውን ለቅቀው እንዳይወጡ በር መቆለፍ ወይም ክልከላ ማድረግ፤
- ስራዎን ለቀው በሚሄዱበት ግዜ፣ በአግባቡ ስላለመያዝዎ ቅሬታ ማቅረብ ወይም ጉዳዩን ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ለማድረግ ወይም እገዛ ለማግኘት ቢሞክሩ በእርስዎ ወይም በቤተሰብ አባላት ላይ ጉዳት ለማስከተል መዛት፤

- እገዛ ለማግኘት ሙከራ ቢያደርጉ ከአገሪቱ ሊባረሩ ወይም በቁጥጥር ስር ሊውሉ እንደሚችሉ ማስፈራራት፤ ወይም
- ለመሄድ፣ ቅሬታ ለማቅረብ፣ ስለሁኔታው ሪፖርት ለማድረግ ወይም እገዛ ለማግኘት የሞከሩ ሠራተኞችን ማስፈራራት ወይም በእነርሱ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ማንም ቢሆን ለማምለጥ ቢሞክር እንደሚገኝና ተመልሶም እንዲመጣ እንደሚደረግ ማስፈራራት።

## ዕዳ

ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ወይም እነርሱን የሚረዱ ሰዎች፣ ያለብዎትን ዕዳ ለማካካስ የጉልበት ሥራ እንዲሰሩ፣ እንዲያገለግሉ ወይም የወሲብ ንግድ ተግባራት (ሴተኛ አዳሪነት) እንዲፈጽሙ ሊጠይቁ ይችላሉ። በዕዳ ምክንያት የጉልበት ሥራ፣ በአገልግሎት ወይም በወሲብ ድርጊት ማሰማራት ወይም ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይሄዱ መከልከል ሕገወጥ ተግባር ነው። ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ዕዳዎን በአንዳች ዘዴ በማብዛት መልሶ ለመክፈል አስቸጋሪ ሊያደርጉትና ዕዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በሕገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎቹ ዘንድ መቆየትን እንዲያስቡ ሊያደርጉዎ ይችላሉ። ዕዳን ማብዛት ለሚለው አገላለጽ ከዚህ የሚከተሉት በምሳሌነት ያገለግላሉ፡-

- ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመክፈል አስቸጋሪ የሆነ ወይም ፈጽሞ የማይቻል እንዲሁም እርስዎ ወደፊት ሊያገኙ ከሚችሉት ገቢ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ዕዳ መጫን፤
- ቀደም ብለው እርስዎ ያልተስማሙበትን ወይም ስምምነት ከተደረገበት ዕዳ በላይ የሆነ ዕዳ መጫን፤
- የሚያገኙትን ገቢ ለዕዳው መክፍያ እንዲሆን አለመስማማት፤
- ዕዳውን ለመክፍል በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪው ዘንድ ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለብዎ በድጋሚ ለመወሰን ፈቃደኛ አለመሆን፤
- ቀደም ብለው እርስዎ ያልተስማሙባቸውን የትራንስፖርት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የምግብ እና ሌሎች ክፍያዎች እና ወጪዎችን መጨመር፤ እና
- ደንብ ባለማክበር፣ በቂ ገቢ ባለማምጣት ወይም በቂ የጉልበት ሥራ ባለመሥራት ወይም አገልግሎት ባለመስጠት ወይም የወሲብ ንግድ ተግባራት ባለመፈጸም ምክንያት ተጨማሪ ክፍያ ወይም ቅጣት መጣል።

## ደንቦች እና ቁጥጥር

ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችና እነርሱን የሚረዱ ሰዎች እርስዎ ካሉበት እንዳይሄዱ፣ ቅሬታዎን እንዳይነግሩ ወይም እርዳታ እንዳይሹ ነገሮችን ከባድ ሊያደርጉ ይችላሉ። ለምሳሌ፡-

- የሥራ ስፍራውን ትቶ መሄድን የሚከለክሉ ደንቦች ሊያወጡ ወይም በሥራ ላይ በማይሆኑባቸው ጊዜያት ወደየት መሄድ እንደሚችሉ ጥብቅ ደንቦች ሊያስቀምጡ ይችላሉ።
- የራስዎን ፓስፖርት፣ የልደት የምሥክር ወረቀት ወይም ሌላ የማንነት መለያ ሰነዶች እርስዎ ዘንድ እንዳያስቀምጡ የሚከለክሉ ደንቦች ሊያወጡ ይችላሉ።
- በቂ ምግብ፣ እንቅልፍ ወይም ሕክምና እንዳያገኙ ሊከለክሉ ይችላሉ፣ ወይም
- ከቤተሰብዎ አባላት፣ ከሌሎች ሠራተኞች፣ ደንበኞች ወይም ሌሎች ከሥራው ስፍራ ውጪ ካሉ ሰዎች፣ ለምሳሌ የሕግ ወይም የማሕበራዊ አገልግሎት ሠራተኞች ጋር እንዳይገናኙ ሊከለክሉ ወይም ገደብ ሊያደርጉ ወይም ሊቆጣጠሩ ይችላሉ።

**ጠቃሚ መረጃ፡** - የአሠሪዎን ተገቢ ያልሆነ አነጋገር እና/ወይም በእርስዎ ላይ የሚወስደውን ተገቢ ያልሆነ እርምጃ እንዲሁም በዚህ ላይ ሊመሰክሩ የሚችሉ ሰዎችን ስሞች እና ስልክ ቁጥር በዝርዝር መዝግበው ይያዙ።

## ማታለል እና ውሸት

ሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችና እነርሱን የሚረዱ ሰዎች ማታለልና ውሸትን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ለምሳሌ፡-

- ስለሥራ ዓይነት፣ የሥራ ሰዓታት፣ የሥራ ወይም የአኗኗር ሁኔታዎች ሃሰተኛ ቃል ሊገቡ ይችላሉ፤
- መጀመሪያ ጥሩ ሥራ እንደሚኖርዎ ቃል ይገቡና በኋላ ግን እጅግ ለረጅም ሰዓታት፣ አስቸጋሪ በሆኑ የሥራ ሁኔታዎች ወይም ቃል ከገቡት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ በሆነ ክፍያ እንዲሰሩ ሊያደርጉ ይችላሉ።
- ጥሩ ሥራ እንደሚኖርዎ ቃል ቢገቡም እንኳን፣ በኋላ ግን በሌላ ዓይነት የጉልበት ሥራ አገልግሎት ወይም የወሲብ ንግድ ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ ለምሳሌ የነርስ ሙያ መምሕር ሆነው እንደሚሰሩ ከነገሩዎ በኋላ የመጠሪያ ድርጅት ውስጥ እንዲሰሩ፣ ወይም በሞግዚትነት እንደሚሰሩ ቃል ከገቡ በኋላ ፈር በለቀቀ ዳንሰኝነት ወይም በወሲብ ንግድ ተግባር ላይ (በሴተኛ አዳሪነት) እንዲሰማሩ ሊያስገድዱዎ ይችላሉ።
- ምንም ዓይነት መብት እንደሌለዎት ሊነግሩዎ ይችላሉ፣
- እርዳታ ለማግኘት ቢሞክሩ ማንም እንደማያምንዎ ወይም ከአገሪቱ ሊባረሩ እንደሚችሉ ይናገራሉ፣ ወይም
- ስለሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪው ማንነት ሃሰት እንዲናገሩ መመሪያ ሊሰጡ ይችላሉ።

## መንገላታትን በማሳወቅዎ ከአገሪቱ ይባረራሉን?

የሰዎችን መንገላታት ለሚያሳውቁ ሰዎች ጥበቃ የሚያደርጉ መርሃ ግብሮች አሉ። ከኢሚግሬሽን ጋር በተያያዘ የሚያሳስብዎ ነገር ቢኖር እንኳን እገዛ ለማግኘት ከመሞከር ወደ ኋላ ማለት የለብዎትም። በእርስዎ አሠሪ ዘንድ ከማይሰራ የኢሚግሬሽን ጠበቃ ማማከር አለብዎ።

የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ሌላ ከፍተኛ የወንጀል ድርጊት፣ ለምሳሌ አስገድዶ መድፈር ወይም የወሲብ ጥቃት ሰለባ እንደሆኑ ካመኑ፣ ለሌላ ዓይነት የኢሚግራንት ያልሆነ ሁኔታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ለምሳሌ "ፐ" (ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች) ወይም "ሀ" (ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ወይም ሌሎች ከፍተኛ የወንጀል ድርጊት ሰለባዎች) ወይም በሌላ መልኩ በዩናይትድ ስቴትስ እንዲቆዩ ሊፈቀድልዎ ይችላል። እነዚህ የኢሚግራንት ያልሆኑ ምድቦች ለድርጊቱ ሰለባዎች ጥበቃ ለማድረግ ሲባል የተቀመጡ ናቸው። በርካታ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ስለ "ፐ" ወይም "ሀ" ኢሚግራንት ያልሆኑ የቆይታ ሁኔታዎች ግንዛቤ የላቸውም፤ ድጋፍ ለሚያደርጉልዎ ሰዎች ስለነዚህ አማራጮች መንገር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

## ለሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠቂዎች ያሉት አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?

- በዩናይትድ ስቴትስ ማእከላዊ መንግስስ ውስጥ ያሉ የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ የሆኑ ሰዎች በፌዴራል ወይም በግዛት መርሃ ግብሮች አማካኝነት ጥቅማ ጥቅሞች እና የኢሚግሬሽን ድጋፍ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ አገልግሎቶች ለእርስዎ ተደራሽ እንዲሆኑ ሊያግዙዎ የሚችሉ በርካታ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን፣ ከአገልግሎቶቹም መካከል የአካላዊ/የጥርስ ሕክምና፣ የአዕምሮ ጤና ሕክምና፣ የመኖሪያ ቤት፣ የኢሚግሬሽን የሕግ እገዛና ሌሎች የሕግ ጉዳዮች፣ የቅጥር ድጋፍና ሕዝባዊ ጥቅማ ጥቅሞች ይካተታሉ።

**ጠቃሚ መረጃ:-** በሥራ ላይ የሆኑባቸውን ጊዜያት ሁሉ በጽሁፍ መያዝ ጥሩ ሃሳብ ነው። ማስታወሻ ደብተር አዘጋጅተው በዚያ ላይ የሰሩባቸውን ቀናት እና ሰዓታት ሁሉ፣ የተከፈለዎትን ክፍያ፣ ክፍያ ያገኙባቸውን ቀናት፣ ማናቸውንም ከክፍያዎ ላይ የተቀነሱ ተቀናሾች እና የተቀነሱበትን ምክንያት ይመዝግቡ።

## ሳምንታዊ የሥራ መመዝገቢያ ናሙና ቅጽ

| ሠራተኛ:- | ተቆጣጣሪ:- |
|---|---|

| ቀን | ተግባራት | ሰዓታት | ክፍያ |
|---|---|---|---|
| | | መግቢያ________________<br>መውጫ ________________<br>ጠቅላላ ________________ | |
| | | መግቢያ________________<br>መውጫ ________________<br>ጠቅላላ ________________ | |



# ለተጨማሪ መረጃ ከዚህ የሚከተሉትን ድረ-ገጾች ይመልከቱ፡-

(ከዚህ የሚከተሉት ድረ-ገጾች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ናቸው )

- የቪዛ ማመልከቻ ሂደት እና የእርስዎ የዩናይትድ ስቴትስ ቪዛ፡- usvisas.state.gov
- ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር፡- www.state.gov/j/tip
- J-1 ቪዛ የልውውጥ መርሃ ግብር፡- j1visa.state.gov
- እኩልነት እና በሥራ ቦታ በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በኃይማኖት፣ በጾታ (እርግዝናን ጨምሮ)፣ በብሔር ማንነት፣ በዕድሜ (40 ዓመት እና ከዚያ በላይ)፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በጄኔቲክ መረጃ ላይ ተመሥርቶ ከመድልዖ ነጻ የመሆንና የመድልዖ ክስ ለማቅረብ፡- www.eeoc.gov
- የሥራ ቦታ ደህንነት መብቶች ወይም ሥራዎ ለደህንነትዎ አደገኛ ነው ብለው ካሰቡና ምርመራ እንዲደረግ ለመጠየቅ፡- www.osha.gov
- ያለተከፈሉ ደሞዝዎን ከአሠሪዎ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ፡- webapps.dol.gov/wow
- ፍትሐዊ ክፍያ ለማግኘት ባለመብት ስለመሆንዎ እና በደመወዝ ጉዳይ ላይ በምን መልኩ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ፡- www.dol.gov/WHD/immigration
- በመኖሪያ ፈቃድ ሁኔታዎ ምክንያት መድልዖ እንዳይደርስብዎ ባለመብት ስለመሆንዎ እና መድልዖን በተመለከተ በምን መልኩ አቤቱታ ማቅረብ እንደሚችሉ፡- www.justice.gov/crt/filing-charge
- ክፍያዎንና የሥራ ሁኔታዎን ለማሻሻል ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በጋራ ኅብረት መመስረት የሚችሉ ስለመሆኑ እና ክስ እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ፡- www.nlrb.gov
- የጤና ኢንሹራንስን በተመለከተ መብቶችዎ፣ ግዴታዎችዎና ልዩ ሁኔታዎች፡- localhelp.healthcare.gov

ይህ በራሪ ፅሁፍ የተዘጋጀው በ2008 በወጣው በክፍል 202 የዊሊያም ዊልበርፎርስ ትራፊኪንግ ቪክቲምስ ፕሮቴክሽን ሪኦቶራይዜሽን ህግ፣ በሕዝባዊ ሕግ 110-457 መሠረት ነው።